በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ - ቤተሰብ

## ክፍል አንድ

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

**E-mail:** kesisolomon4@gmail.com

*ቦታ፡-* ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

በየሳምንቱ ረቡዕ ምሽት ከ12፡30 – 1፡30

**ሚያዝያ ፲፱ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.**

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## ***መግቢያ***

- **እግዚአብሔር ለቤተሰባዊ ሕይወት ልዩ ትኩረት በመስጠት ለጋብቻ ሕይወት ታላቅ መሰረት ጥሏል፡፡**
- ***ይህንም***

1. ***አዳምን በአምሳሉና በአርአያው በመፍጠሩ*** ‹‹እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር... እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።» ***ዘፍጥ 1፡26-27፡፡***
2. ***ጋብቻንና ልጆች መውለድን በመባረኩ*** ‹‹እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው።» ***ዘፍጥ 1፡28፡፡***
3. ***ሔዋንን በመፍጠሩ፡- እግዚአብሔር ሔዋንን ከአዳም አሳንሶ ሳይሆን*** ‹‹እግዚአብሔር አምላክም አለ፦ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም የሚመቸውን ረዳት እንፍጠርለት።» ***ዘፍጥ 2፡18፡፡*** **እንዳለው የምትተካከለው ረዳት አድርጎ ፈጠራት፡፡ እግዚአብሔር ሔዋንን ከአዳም ጎንም በመፍጠሩ ከአዳም የምትካከል ብቻ ሳትሆን አካሉ፣ አጥንቱ፣ ሥጋዋም ከሥጋው የሆነች መሆንዋን አረጋግጧል፡፡** « እግዚአብሔር አምላክም ... ወደ አዳምም አመጣት።» ***ዘፍጥ 2፡22፡፡*** **እንደተባለው ወደ አዳም ያመጣት እግዚአብሔር ስለሆነ ክብር ለሔዋን ሆነ፡፡ ጋብቻም እግዚአብሔር የፈጠረው ስለሆነ ከበረ፡፡ አዳምም አካሉ በመሆንዋ ብቻ ሳይሆን ከእግዚአብሔር የተሰጠችው በመሆንዋ ደስ ተሰኝቶ** « አዳምም አለ፦ ይህች አጥንት ከአጥንቴ ናት፥ ሥጋም ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል።» ***ዘፍጥ 2፡23*** **ብሎአል፡፡**

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

***መግቢያ…***

**<u>የትዳር ሕይወት አስፈላጊነት</u>**

1. *ጋብቻን አስመልክቶ* ‹‹ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል፥ በሚስቱም ይጣበቃል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ።›› ***ዘፍጥ 2፡24፡፡*** ብሎ እግዚአብሔር ከእውነተኛ ረዳት ጋር አንድ ማድረግ ስለሚቻለው ምስጢሩ ነግሮናል፡፡

2. እግዚአብሔር ለጋብቻ ታላቅ ጥንቃቄ አድርጓል፡፡ ይህም አምላካችን በመዋዕለ ሥጋዌው በሠርግ ቤት በመገኘት ጋብቻውን በመባረክ ገልጦታል፡፡ ***ዮሐ 2፡1-11፡፡***

3. ቤተክርስቲያንም ለጋብቻ ምስጢር ልዩ ትኩረት ትሰጣለች፡፡ ከዚህም የተነሳ ምስጢሩን በጸሎትና በአስተምህሮዋ የታጀበ በማድረግ የምስጢሩን ታላቅነት ትገልጣለች፡፡ ምስጢሩ ሲፈጸምም በፍጥረት መጀመሪያ የመጀመሪያዎቹን ተጋቢዎች እንደባረከ መንፈስ ቅዱስ ጋብቻውን ለመባረክ ይመጣል፡፡ ***ዘፍጥ 2፡23*** ስለዚህ ለተወደዱ ወጣት ወንዶችና ሴቶች እንዲሁም ለተቀረነውም ሁሉ ጥልቅ ግንዛቤ ይኖረን ዘንድ ቅዱስና በሕይወታችንም ተፈላጊ ስለሆነው የጋብቻ ሕይወት መርሆዎች እናስተምራለን፡፡ ‹‹ይህ ምሥጢር ታላቅ ነው›› ***ኤፌ 5፡32፡፡***

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## *ክፍል አንድ - ትዳርን የተዋጣለት የሚያደርጉት ምክንያቶች*

- **የሕይወት አጋራችንን ስንመርጥ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ምንድር ናቸው?**

  1. አጠቃላይ ትኩረቶች

  - የትዳር አጋርን ለመምረጥ ረጅም ዘመናት ወስዶብን ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን የሕይወት አጋራችንን የምንመርጠው በምን መመዘኛ ነው? ፍጹም የሆነውን/ችውን እንፈልጋለን ወይስ ለተወሰኑ ጉዳዮች ብቻ ትኩረት ሰጥተን ሌሎች ጉዳዮችን በቸልታ እንተዋቸዋለን?
  - ወንዱ ሰው የመንፈሳዊውን ውበት አስፈላጊነት ዘንግቶ እጅግ ውብ የሆነችውን ልጃገረድ ሊያፈላልግ ይችላል፡፡ ሌላው ሰው ደግሞ ገንዘብን የሚያገባ ይመስል ሀብትን ሊመለከት ይችላል፡፡
  - ሰው የወደፊት የሕይወት አጋሩን ለተጋቢዎቹ ስምምነት አስፈላጊ የሆኑትን መሠረታዊ ነገሮች ዘንግቶ ብዙም አስተዋጽኦ በማይኖራቸው በትምህርት፣ በዕድሜ፣ በልጅቱ ቤተ ሰቦች ታዋቂነት ላይ አትኩሮት በማድረግ በእውር ድንብር አጋሩን በማፈላለግ ጉልበቱን የሚጨርስ ሊሆን ይችላል፡፡
  - እንዲሁም የሚያፈቅር ታጋሽ ልብ ወይም መልካም ሥነ ምግባር ያላትን ከማፈላለግ ይልቅ ብዙ ቁሳዊ ሀብት ያላትን የሚያፈላለግ ወይም ሌላው/ሌላዋ ደግሞ ወደ ሠለጠነው ዓለም ለመሰደድ የምትሆነውን/የሚሆነውን የሚያፈላልጉ ይኖራሉ፡፡
  - እነዚህ ሁሉ አካሄዶች የሕይወት አጋርን በመምረጥ ሂደት የሚያስፈልጉትን ትኩረቶችን በአግባብ ማሳወቅና ማወቅን ስለሚሹ እንደሚከተለው እንመለከታቸዋለን፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## 1. ውበትን ለማግባት ለሚሹ የሚከተሉትን እንመክራለን፡፡

- አካላዊ ደም ግባትን ብቻ ሳይሆን በሌሎች ነገሮች ያለ ውበትንና መልካምነትን መመልከት ይገባል፡፡
- ከተክለ ቁመናና ከመልክ (ቀለም) ጥበብን እናስቀድም!!!
- በአጠቃላይ ከአካላዊው ደም ግባት በፊት መንፈሳዊነትንና ጤናማ የሆነ አመለካከትን ማስቀደም ያስፈልጋል፡፡ ጠቢቡ ሰሎሞን ‹‹ውበት ሐሰት ነው፥ ደም ግባትም ከንቱ ነው እግዚአብሔርን የምትፈራ ሴት ግን እርስዋ ትመሰገናለች።›› ***ምሳ 31፡30፡፡*** እንዳለ፡፡
- ወንዶች ሴቶችን እጅግ ሊያኮራቸው የሚችለውን አካላዊ ውበታቸውን ወይም ደም ግባታቸውን ሳይሆን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ለማደግ የምትረዳንን የርስዋም ሆነ የቤታችሁ ራስ መሆንህን ልትቀበል የምትችልበትን ቀና ልቦናዋን መመልከት ይገባቸዋል፡፡ በመልካምነትዋ ጥበብ ይገኝባታልና፡፡ ‹‹ ልበ ጠማሞች በእግዚአብሔር ዘንድ አስጸያፊዎች ናቸው በመንገዳቸው ፍጹማን የሆኑ ግን የተወደዱ ናቸው።›› ***ምሳ 11፡20፡፡***
- ወዲያው ስትላመደው እንደ ተለመደ ነገር ልትቆጥረው የምትችለውን አካለዊ ደምግባትን ብቻ አትመልከት፡፡ ምክንያቱም ኩራታቸውን፣ ትምክህታቸውን በመንፈሳዊ ሕይወት የሚኖር ደካማነታቸውን ተለማምደህ ልትታገሰው አትችልምና፡፡
- በውጪ ስንታይ ለምንመስለው ሳይሆን ለፈቃዳችን ወይም ለፍላጎታችን ተገቢውን ጥንቃቄ የሚያደርግ/የምታደርግ የሕይወት አጋር ይኑረን፡፡
- ውበት ከእግዚአብሔር የተሰጠ ስጦታ ቢሆንም በበርካታ አቅጣጫዎች ስጦታው ያላቸውን መመልከት ከእነርሱም መካከል የመንፈስቅዱስ ስጦታና ፍሬ ‹‹ ፍቅር፥ ደስታ፥ ሰላም፥ ትዕግሥት፥ ቸርነት፥ በጎነት፥ እምነት፥ የውሃት፥ ራስን መግዛት›› ***ገላ 5:22፡፡*** የበዛለትን/የበዛላትን መምረጥ ይገባል፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## 2. የሕይወት አጋራቸውን ሲመርጡ ስሜታቸው ለሚከተሉ ሁሉ የሚከተለውን እንመክራለን፡፡

- ብሩህ በሆነ አእምሮ ስሜታችንን እንቆጣጠር እንጂ ስሜታችን ይነዳን ዘንድ አንፍቀድለት፡፡
- ስሜታችን ምክንያታዊና ግልጽ የሆነ ሊረዱት የሚያስችል ሐሳብ ይኑረው፡፡
- ስለ ጋብቻ ሕይወት ስናስብ ውሳኔአችን ስሜት ላይ ብቻ የተደገፈ እንዳይሆን አስቀድመን በአግባቡ እናስብበት፣ ሌሎችም ሐሳባቸውን እንዲያጋሩን ዕድል እንስጣቸው፡፡
- በጓደኝነት የቀረብናቸውን ሁሉ ለሕይወት አጋርነት ማሰብ አግባብነት ያለው አይሆንም፡፡ አስቀድመን ሁሉንም ጓደኛ እናደርግ ዘንድ የመራን ምክንያት ምን ነበር? ጓደኛን የሕይወት አጋር ብናደርግ ምቾት ይሰማናል? እንደ ጓደኛ የወደድነው ነገር እንደ ሕይወት አጋር ሲወሰድ ብዙ የሚስብ ላይሆን ይችላልና፡፡ ስለዚህ ትክክለኛ ውሳኔ መወሰን እንዲያስችለን አስቀድመን በማስተዋል እናስብ፡፡
- የተወደዳችሁ ክርስቲያኖች መንፈሳዊና ማኅበራዊ መደላደልን ለማግኘት እንዲያስችለን ከቤተ ክርስቲያን የምናገኛቸውን ምርጫችን አድርገን እናስቀድም፡፡
- ነገር ግን በውጪ ደም ግባታቸው ተማርከን በዚህን ዓለም ፈቃድ የተያዙትን ማግባት ያለ ምንም ጥርጥር ለተወሰነ ጊዜ የፈለግነውን ስሜታዊ እርካታ ሊያስገኙልን ቢችልም፣ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ስንዝል ግን አለመረጋጋት አጅቦ ይከበናል፡፡
- የዚህን ዓለም ፈቃድ የሚያደርጉትን ከማግባት እንቆጠብ፡፡ ምክንያቱም ምንም ያህል ብንቀራረብ ከቤተ ክርስቲያን አውጥተው ወደ ዓለም ይመሩናልና፡፡
- ከቤተ ክርስቲያን የሆኑት ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ይስቡናል ወደ እግዚአብሔርም ያቀርቡናል ሕይወታችንንም ለዘላለማዊ ሕይወት የተዘጋጀች ያደርጋሉ፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

3. ***የሕይወት አጋራቸውን ሲመርጡ ሀብትን ወይም ባለጠግነትን ለሚመለከቱ ሁሉ***

- ታላቅ ከሆነ ባለጠግነቱ ባሻገር ‹‹ጥበብ ከቀይ ዕንቍ ትበልጣለችና የከበረ ነገር ሁሉ አይተካከላትም፡፡›› ***ምሳ 8፡11፡፡*** ያለንን የጠቢቡ ሰሎሞንን ምክር ልብ እንበል፡፡
- እጅግ መልከ መልካም የነበረችው አቢግያ እጅግ ባለጠጋ ለሆነው ሰው ከተዳረች በኋላ እውነተኛ ውበትዋ አእምሮዋና ጥበብዋ ስለነበር ቅዱስ መጽሐፍ ‹‹ወደ ደም እንዳልሄድ፥ በእጄም በቀል እንዳላደርግ ዛሬ የከለከለኝ አእምሮሽ የተመሰገነ ይሁን፥ አንቺም የተመሰገንሽ ሁኚ፡፡›› በማለት አመስግኖአታል፡፡ ***ቀዳ ሳሙ 25፡33፡፡*** ልበ አምላክ ዳዊትም ባገባት ጊዜ ከባለጠግነትዋና ከውበትዋ በላይ የአእምሮዋን ታላቅነት ቅድሚያ ሰጥቶታል፡፡
- ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍ ‹‹ልባም ሴትን ማን ሊያገኛት ይችላል? ዋጋዋ ከቀይ ዕንቍ እጅግ ይበልጣል፡፡›› ***ምሳ 31፡10፡፡*** የተባለላትን ባለጠግነትዋ ከገንዘብ ይልቅ በጥበብዋ የሆነችዋን የሕይወት አጋራችን አድርገን እንምረጥ፡፡
- ጥበብ ከባለጠግነት ሊመነጭ ቢችልም ባለጠግነት ግን ጥበበኛነትን ፈጽሞ አያረጋግጥም፡፡ ‹‹ ብልሃተኛ ሴት ቤትዋን ትሠራለች ሰነፍ ሴት ግን በእጅዋ ታፈርሰዋለች፡፡›› ***ምሳ 14፡1፡፡***
- ጥበበኛ ሴት ባለጠጋ እንድንሆን ምክንያት ልትሆን ስትችል ጥበብ የጎደላት ባለጠጋ ሴት ግን የመንፈሳዊ ሕይወታችንን ሀብት ልታሳጣን ትችላለች፡፡

# ኦርቶዶክሳዊ ቤተሰብ

## በሚከተሉት ነገሮች ከእኛ ልትገጥም የምትችል የሕይወት አጋር እንምረጥ

### *ዕድሜ*

- በትዳር የተረጋጋን መሆን ያስችለን ዘንድ ጋብቻን በትክክለኛው ጊዜ እናስብ፡፡
- በአእምሮ፣ በስሜት፣ በገንዘብ አቅም፣ በመንፈሳዊነትም እስክንበስል ድረስ ከማግባት እንታገስ፡፡ ብስለትን ካገኘን ከጋብቻው ጋር የሚመጣ ኃላፊነትን መቀበል እንችላለን፡፡
- ለወንዶች ለጋብቻ የሚሆነው ዕድሜ (አቅመ አዳም ሠላሳ ዓመት ቢሆንም) እንደ ትምህርት ደረጃችን፣ አስተዳደጋችንና አስተሳሰባችን ለጋብቻ የምንበቃበት ዕድሜ ይወሰናል፡፡
- ልጃገረዶችን በተመለከተ ግን የሚከተሉት ነገሮች ዕሜዋን (አቅመ ሔዋን) ይወስናሉ፡፡
    - **ለጋብቻ በሚስማማ ተገቢ ዕድሜ ላይ መሆንዋ፡-** የቤተሰባዊ ሕይወትን ኃላፊነት ለመቀበል የተዘጋጀች ለዚያም የሚመጣጠን ዕድሜ ያላት መሆን፡፡ ለራስዋ ሕይወት ኃላፊነት መውሰድ የማትችል ልጃገረድ በቅጽበት የቤተሰብን ሕይወት ኃላፊነት ትወስዳለች ብሎ ማሰብ አስቸጋሪ ነው፡፡
    - **ልጅ ለመውለድ የሚያስችላት ትክክለኛ ዕድሜ፡-** ይህም ማለት በወጣትነት ወይም በእርጅና ለመውለድ ያለመቻልንና እናትንም ሆነ ጽንሱንም ሊያጋጥሙ የሚችሉ ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ነው፡፡
    - **ከባልዋ ዕድሜ ጋር የተመጣጠነ ልዩነት ባለው ዕድሜ፡-** ወንዱ ከልጃገረድዋ ያለው የዕድሜ ልዩነት እጅግ ከፍተኛ ከሆነ እንደ ሚስቱ ሳይሆን እንደ ሴት ልጁ ሊቆጥራትና የሴት ልጅ ክብካቤ ሊያደርግላት ይችላል፡፡ ይህም ‹‹ለርሱ የምትሆነው ረዳት›› *<u>ዘፍጥ 2፡18፡፡</u>* እንዳትሆን ይገድባታል፡፡ መመህም ብቻ ሳይሆን እንደ ባል ሳይሆን እንደ አባት ሆኖ ስሜትዋን የመረዳት ክፍተት ይፈጥራል፡፡ የልጃገረድዋም ዕድሜ ከባልየው እጅግ ከፍ ያለ ልዩነት ያለው መሆን የለበትም፤ ምክንያቱም በርካታ ሥነ-ልቦናዊ ክፍተቶችን ይፈጥራልና፡፡
    - ስለዚህ ወደ ጋብቻ ሂደት ከመግባታችን በፊት የሕይወት ምርጫ ያደረግነው አጋር በዕድሜ የምትመጣጠንና ዕድሜ በፈጠረው ተጽእኖ የተነሳ ለመውለድም የምትችል መሆን አለመሆንዋን በአግባብ እንመርምር፡፡

For your queries or questions E-mail:
kesisolomon4@gmail.com

To get all the lessons, surf :
www.zeorthodox.org

ይቆየን።